የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No.46
ADDIS ABABA 3rd July, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፭/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለአዳማ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ክፍል ሁለት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፮ሺ፰፻፺፱

**CONTENTS**

**Proclamation No. 795/2013**

**Export-Import Bank of China Loan Agreement for Financing the Adama Wind Power Construction Project (Phase II) Ratification Proclamation ............................... Page 6899**

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፭/፪ሺ፭**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአዳማ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ክፍል ሁለት ማስፈጸሚያ የሚውል ፪፻፺፫ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺ. የአሜሪካን ዶላር (ሁለት መቶ ዘጠና ሦስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ. የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ ማርች ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**PROCLAMATION No. 795/2013**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF CHINA**

WHEREAS, Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China stipulating that the Export-Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amounting to 293,250,000 USD (two hundred ninety three million two hundred fifty thousand United States Dollars) for financing the Adama Wind Power Construction Project (Phase II) was signed in Addis Ababa on the 27th day of March, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 11th day of June, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ዱ ዋጋ
it price 2.30

www.chilot.me

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዳማ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ክፍል ሁለት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፭/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ ማርች ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር PBC No. 2013 (14) Total No. (258) 142030305201321O334 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፺፫ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺ የአሜሪካን ዶላር (ሁለት መቶ ዘጠና ሦስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export-Import Bank of China Loan Agreement for Financing the Adama Wind Power Construction Project (Phase II) Ratification Proclamation No. 795/2013".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No. PBC No. 2013(14) Total No. (258) 142030305201321O334 signed in Addis Ababa on the 27th day of March, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export–Import Bank of China is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 293,250,000 USD (two hundred ninety three million two hundred fifty thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of July, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

www.chilot.me